የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፭
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.35
ADDIS ABABA 20th April, 2020

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፷፮/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፫/፪ሺ፲፪ ማስፈፀሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ……….ገጽ ፲፪ሺ፭፻፪

## Content

Regulation No.466/2020

State of Emergency Proclamation No. 3/2020 Implementation Regulation....................Page 12,502

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፷፮/፪ሺ፲፪**

**<u>የኮቪድ-፲፱ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፫/፪ሺ፲፪ ማስፈፀሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ ፺፫/፬/(ሀ) እና የኮቪድ-፲፱ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ በወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፫/፪ሺ፲፪ አንቀፅ ፬/፩/ መሰረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የወረርሽኙ ሥርጭት እያስከተለ ያለውንና ሊያስከትል የሚችለውን ሰብዓዊ፣ ማኅበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳቶች ለመቀነስ እና ለመከላከል የመብት እገዳዎችንና፣ እርምጃዎችን በሚያወጣቸው ደንቦች እንደሚወስን በመደንገጉ፤

ይህን ተከትሎ የተከለከሉ ተግባራትን፣ የሚወሰዱ እርምጃዎችንና የመብት እገዳዎችን በዚህ ደንብ መደንገግ በማስፈለጉ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር ፫/፪ሺ፲፪ አንቀፅ ፬/፩/ መሰረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል::

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No.466 /2020**

**<u>A REGULATION ISSUED TO IMPLEMENT THE STATE OF EMERGENCY PROCLAMATION NO. 3/2020 ENACTED TO COUNTER AND CONTROL THE SPREAD OF COVID-19 AND MITIGATE ITS IMPACT</u>**

In Accordance with, Article 93(4)( a) of the FDRE Constitution and Article 4(1) of the *State of Emergency Proclamation No. 3/2020 Enacted to Counter and Control the Spread of COVID-19 and Mitigate Its Impact* which provides that the Council of Ministers shall stipulate, through Regulations it will adopt, details of the suspension of rights and measures to be taken to counter and mitigate the humanitarian, social, economic and political damage that could be caused by COVID-19;

WHERE AS, it has become necessary to provide the particulars of measures to be adopted and the rights to be suspended in a Regulation;

NOW,THEREFORE, this Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 4(1) of Proclamation No 3/2020.

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፫/፪ሺ፲፪ ማስፈፀሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፷፮/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. ትርጓሜ

**ለዚህ ደንብ ዓላማ፡-**

፩/ **"አዋጅ"** ማለት የኮቪድ-፲፱ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፫/፪ሺ፲፪ ነው፤

፪/ **"የሚኒስትሮች ኮሚቴ"** ማለት በዚህ ደንብ አንቀፅ ፭ የተቋቋመው ኮሚቴ ማለት ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ፣ በኮሚቴው የሚቋቋሙና ውክልና የሚሰጣቸው በፌደራል፣ በክልሎች፣ በከተማና በወረዳ ደረጃ ያሉ ንዑሳን ኮሚቴዎችንም ያካትታል፤

፫/ **"ስብሰባ"** ማለት ማንኛውንም ተግባር ለመፈጸም፣ ለመነጋገር፣ ለመወያየት ወይም መሰል ተግባራትን ለማከናወን የአንድ ቤተሰብ አባላት ከሆኑ ውጪ አራትና ከዚያ በላይ ሆኖ በአንድ ቦታ በአካል መገኘት ነው፤

፬/ **"ኳራንታይን"** ማለት በኮቪድ-፲፱ ተይዘዋል ተብለው የሚጠረጠሩ ሰዎችን በቫይረሱ መያዝ አለመያዛቸው እስኪረጋገጥ ድረስ በተለየ ቦታ እንዲቆዩ ማድረግ ነው፤

፭/ **"ለይቶ ማቆየት"** ማለት በኮቪድ-፲፱ መያዙ የተረጋገጠ ሰው ቫይረሱን ወደ ሌሎች ሰዎች እንዳያስተላልፍ ከቫይረስ ነፃ እስኪሆን ድረስ ለብቻው ለይቶ እንዲቆይ ማድረግ ነው፤

፮/ **"ሀገር አቋራጭ የህዝብ ትራንስፖርት"** ማለት ከአንድ ክልል ከተማ ወደሌላ ክልል ከተማ የሚደረግ ማንኛውም የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሲሆን በአንድ ክልል ውስጥ ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ የሚደረግ የህዝብ ትራንስፖርትንም ያጠቃልላል፤

## 1. Short Title

This Regulation may be cited as "*State of Emergency Proclamation No. 3/2020 Implementation Regulation No.466/2020*".

## 2. Definition

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1/ "**Proclamation**" means the "*State of Emergency Proclamation Enacted to Counter and Control the Spread of COVID-19 and Mitigate Its Impact Proclamation No. 3/2020.*"

2/ "**Ministerial Committee**" means the ministerial committee established in accordance with Article 5 of this Regulation and includes sub- committees to be established by the Committee and delegated at the Federal, Regional, Municipal and Woreda level;

3/ **"Meeting"** means gathering of four or more persons who do not belong to a single family, in one place for the purpose of collectively carrying out any activity, discussion or any similar purposes;

4/ **"Quarantine"** means separation of persons who are suspected to be exposed or infected with Covid-19 until it is ascertained whether they are infected with the virus or not;

5/ **"Isolation"** means separation of a person who is Covid-19 positive until he recovers from the virus to ensure that he will not infect other persons;

6/ **"Cross Country Public transportation"** means any form of public transit between two cities in one Regional State or between cities in two Regional States;

፯/ **"የከተማ ውስጥ የህዝብ ትራንስፖርት"** ማለት በከተማ ውስጥ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ታክሲዎችን፤ አውቶብሶችና የፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት አውቶብሶችን ያጠቃልላል፤

፰/ **"መጠጥ ቤት"** ማለት በግልፅ የሆቴልነት ስያሜ ከተሰጠው ቤት ውጪ ያለ ማናቸውም ዓይነት የአልኮል መጠጥ የሚሸጥበት ቤት ነው፤

፱/ **"ለማህበራዊ ዓላማ"** ማለት ሰርግ፣ለቅሶ፣ ክርስትና፣ልደት፣ እድር እና ለመሳሰሉት ዓላማ ማለት ነው፣

፲/ **"ፍትህ አካላት"** ማለት፣ የፌደራልና ክልል ፖሊስና ዐቃቤ ህግ ተቋማትና ፍርድ ቤቶች ማለት ነው፣

፲፩/ በአዋጁ ላይ የተሰጡ ሌሎች ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ::

## ፫. የተከለከሉ ተግባራት

፩/ ለሃይማኖታዊ ወይም ማህበራዊ ዓላማ፣ ለመንግስታዊ ወይም ፖለቲካዊ ስራ ወይም ሌላ መሰል ዓላማ አምልኮ በሚደረግባቸው ቦታዎች፣ በመንግስት ተቋማት፣ በሆቴሎች፣ በማናቸውም የመሰብሰቢያ አዳራሾችና በማናቸውም ቦታ ስብሰባ ማድረግ የተከለከለ ነው።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አስገዳጅ ሁኔታዎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ የሚኒስትሮች ኮሚቴ ወይም በኮሚቴው የሚቋቋሙና ውክልና የሚሰጣቸው በክልሎች፣ በከተማና በወረዳ ደረጃ ባሉ ንዑሳን ኮሚቴዎች ስብሰባ እንዲደረግ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፫/ ማንኛውም ሰው ለሰላምታና ሌላ ማንኛውም ;aላማ በእጅ መጨባበጥ ክልክል ነው።

፬/ ማንኛውም ሀገር-አቋራጭ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሰው በማንኛውም ጊዜ ከተሸከርካሪው ወንበር ብዛት ፶% በላይ ሰዎችን ጭኖ መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው።

7/ **"Inter-City Public transportation"** means public transit in cities including taxies, buses, and shuttle services for public servants.

8/ **"Bar"** means any establishment other than hotels which serves alcoholic drinks.

9/ **"Social purpose"** includes gatherings for weddings, wakes, christenings, birthdays, self-help associations, or similar events.

10/ **"Justice Organs"** means Federal and Regional police, Prosecutorial and Judicial institutions.

11/ Definitions provided in the Proclamation are applicable to this Regulation.

## 3. Prohibited Activities

1/ It is prohibited to conduct meetings for religious, government, social or political purposes in places of worship, public institutions, hotels, meeting halls or any other place .

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, in circumstances where there are compelling reasons, the Ministerial Committee or sub committees to be established by the committee at federal, regional, municipal and Woreda levels many grant permissions for holding meetings.

3/ It is prohibited for any person to shake hands with another as a greeting or for any other purpose.

4/ It is prohibited for any cross country public transport service provider to carry passengers greater than 50 % of the seating capacity of the vehicle.

፭/ ማናቸውም የከተማ ውስጥ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ታክሲ፣ አውቶቡስ፣ የፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት አውቶቡስ ከተሽከርካሪው የወንበር ቁጥር ፶% በላይ ሰዎችን ጭኖ መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው።

፮/ ማንኛውም የግል ተሽከርካሪ ሾፌሩን ሳይጨምር ከተሽከርካሪው የወንበር ቁጥር ፶% በላይ ሰዎችን ጭኖ መንቀሳቀስ ፤ እንዲሁም በባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎች እና በጋሪዎች ከአሽከርካሪው ውጪ ከአንድ ሰው በላይ መጫን፣ እንዲሁም በሞተር ሳይክል ከአሽከርካሪው ውጪ ሌላ ሰው መጫን የተከለከለ ነው፡፡

፯/ የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ከዚህ በፊት ሲጭን ከነበረው አቅሙ ፳፭% በላይ ሰዎችን ጭኖ መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው።

፰/ የኢትዮ-ጂቡቲ የምድር ባቡር ከወንበር ቁጥሩ ፶% በላይ ሰዎችን ጭኖ መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው፡፡

፱/ ማንኛውንም ታራሚን ወይም ተጠርጣሪን በአካል በመገኘት በማረሚያ ቤት ወይም ፖሊስ ጣቢያ መጠየቅ ክልክል ነው፤ ሆኖም ይህ ድንጋጌ በፖሊስ ጣቢያ ለሚገኝ ተጠርጣሪ ከተጠርጣሪው ጋር በአካል ሳይገናኙ ስንቅ ማድረስን አይከለክልም።

፲/ በጭፈራ ቤቶችና በመጠጥ ቤቶች ማናቸውንም የመጠጥና መዝናኛ አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

፲፩/ በማናቸውም ቦታ የሺሻ ማስጨስና ጫት ማስቃም አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው።

፲፪/ የሲኒማ፣ ቲያትር ወይም በአንድ ቦታ ብዙ ሰዎችን የሚያሰባስቡ መሰል የመዝናኛ አገልግሎቶችን መስጠት ክልክል ነው።

፲፫/ ሆቴሎች፣ ካፌዎች ወይም ምግብ ቤቶች አገልግሎት በሚሰጡበት ጊዜ በአንድ ጠረጴዛ ላይ ከሶስት ሰው በላይ እንዲቀመጥ ማድረግ የተከለከለ ሲሆን ተገልጋዮች በሚቀመጡባቸው ጠረጴዛዎች መካከል ያለው ርቀትም ሁለት የአዋቂ እርምጃ መሆን አለበት፤ ሆኖም ተገልጋዮች የሚገለገሉት

5/ It is prohibited for any inter-city transport service provider including shuttle services for public servants to carry passengers greater than 50 % of the seating capacity of the vehicle.

6/ It is prohibited for any driver of a private automobile to carry passengers greater than 50 % of the seating capacity of the vehicle excluding the driver and it is also prohibited for auto rickshaws and horse drawn carriages to carry more than one passenger or for motorcycles to carry anyone other than the motorist.

7/ It is prohibited for the Addis Ababa light railway to carry passengers greater than 25 % of the number of passengers it used to serve previously.

8/ It is prohibited for Ethio- Djibouti railway to carry passengers greater than 50 % of its seating capacity.

9/ It is prohibited to visit any detainee in prisons or at a police station. However, delivery of provisions for suspects detained at police stations, without having any physical contact with the detainee is not prohibited.

10/ It is prohibited to serve alcohol or recreational services at night clubs and bars.

11/ It is prohibited to operate establishments that serve shisha and khat.

12/ It is prohibited to provide entertainment services at cinemas, theatres or any such place where a large number of people will be assembled.

13/ Hotels, restaurants and cafes shall not provide services to more than three patrons at a single table and should ensure that tables which are being used by patrons simultaneously are at least two adult strides apart. If patrons are served without tables, they have to maintain a distance of two adult strides.

በጠረጴዛ ላይ ካልሆነ በመካከላቸው የሚኖረው ርቀት ሁለት የአዋቂ እርምጃ መሆን አለበት።

፲፬/ በድንበር አካባቢዎች በሚገኙ ኬላዎች በኩል ወደ ሀገር ውስጥ መግባትም ሆነ ወደ ውጪ መውጣት፣ ከህጋዊ ደረቅ እና ፈሳሽ ካርጎ ውጪ እቃ ማስገባት እና ማስወጣት የተከለከለ ነው።

፲፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፲፬ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በውጪ ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በኬላዎች በኩል ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ የሚኒስትሮች ኮሚቴ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።

፲፮/ ለዚሁ ዓላማ ከተቋቋመው ኮሚቴ ወይም በተመሳሳይ መልኩ በክልሎች ደረጃ በሚቋቋሙ ንዑስ ኮሚቴዎች ወይም ተመሳሳይ አደረጃጀቶች አማካኝነት ፈቃድ ከተሰጠው ሰው ውጪ በማንኛውም የክልልም ሆነ የፌደራል መንግስት ባለስልጣን ወይም ባለሙያ ኮቪድ-፲፱ኝን በተመለከተ የፌደራል ወይም የክልል መንግስትን ወክሎ መግለጫ መስጠት የተከለከለ ነው።

፲፯/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፲፮ የተመለከተው ክልከላ ቫይረሱን አስመልክቶ የወጡ ህጎችን በተመለከተ የሚደረግ የሙያ ትንተናን ወይም በህክምና ባለሙያዎች የሚደረጉ ማብራሪያዎችን ወይም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በየእለቱ የሚሰጡ መረጃዎችን አይመለከትም።

፲፰/ ማንኛውም የመኖሪያም ሆነ የንግድ ድርጅት ቤት አከራዮች በተከራዩ ስምምነት ካልሆነ በስተቀር ቤቱን እንዲለቅ ማድረግ ወይም የቤት ኪራይ ዋጋ ጭማሪ ማድረግ የተከለከለ ነው።

፲፱/ ማናቸውም በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፮/፪ሺ፲፩ መሰረት የሚተዳደሩ ሰራተኞችን የሚያስተዳድሩ የግል ድርጅቶች በስራቸው ያሉ ሰራተኞችን የስራ ውል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚያስቀምጠው ሥርዓት ውጪ ማቋረጥ የተከለከለ ነው።

14/ It is prohibited to enter into or exit from the country or import and export anything other than legal dry or liquid cargo through inland entry ports.

15/ Without prejudice to Sub-Article (14) of this Article, the Ministerial Committee may grant permission for Ethiopians to enter the country through inland entry ports.

16/ Without the permission of the committee established for this purpose at the federal level or subcommittees established for this purpose by the federal government at the regional level or equivalent entities of regional administrations; no regional or federal official or expert can give statements representing the federal or regional government to the press about COVID-19.

17/ The prohibition under Sub-Article (16) is not applicable to professional commentary on laws enacted in relation to COVID-19 or professional medical explanations or the daily press briefings of the Ministry of Health.

18/ It is prohibited for any lessor of residential or commercial property to evict a lessee or increase rent without the consent of the lessee.

19/ It is prohibited for organizations covered by Proclamation No 1156/2019 to terminate employment contracts except in accordance with the protocol established by the Ministry of Labour and Social Affairs.

፳/ ማንኛውም የመንግስትም ሆነ የግል ትምህርት ተቋም በትምህርት ቤት ወይም በሌላ ማናቸውም ቦታ አስተማሪና ተማሪዎች በአካል ተገናኝተው መማር ማስተማር ስራ እንዲሰራ ማድረግ ወይም ማስተማር የተከለከለ ነው፡፡

20/ It is prohibited for any public or private school or educational institution to conduct classes face to face in schools or campuses or in any other place.

፳፩/ ማንኛውም ሁለትና ከዚያ በላይ ሰው በመሆን የሚጫወቱባቸውን ጨዋታዎች፣ ለህዝብ ክፍት በሆነ ቦታ ማጫወትም ሆነ መጫወት የተከለከለ ነው፡፡

21/ It is prohibited to play or provide facilities for others to play games where two or more persons participate in any public place.

፳፪/ ማናቸውንም የስፖርት ውድድሮች ወይም የቡድን ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ የተከለከለ ነው።

22/ It is prohibited to engage in sport competitions or any group sport activities.

፳፫/ ለህዝብ ክፍት በሆኑ የህፃናት ማጫዎቻ ቦታዎች አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው።

23/ It is prohibited to provide to the public playground services.

፳፬/ ማንኛውም ሰው የባንክ አገልግሎት በሚሰጥባቸው አካባቢዎች፣ በገበያዎች፣ በትራንስፖርት መሳፈሪያ ቦታዎች፣ በሱቆች፣ በመድሀኒት መሸጫ አካባቢዎች፣ ህዝባዊ አገልግሎት በሚሰጥባቸው ቦታዎችና ሌሎች ህዝብ በሚበዛባቸው መሰል አካባቢዎች ከሁለት የአዋቂ እርምጃዎች በታች በሆነ ርቀት መቆምም ሆነ መቀመጥ የተከለከለ ነው፡፡

24/ Any person who is being served at banks, market places, transport stations, shops, pharmacies or any other place providing services to the public shall stand or seat at least two adult strides away from any other person.

፳፭/ መሰረታዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት እንደ መብራት ሀይል፣ ከውሃ አቅርቦት ጋር ግንኙነት ያለው ስራ የሚሰሩ ተቋማት ፣ ኢትዮ ቴሌኮም፣ የህክምና ተቋማት፣ ባንኮች፣ ከምግብ አቅርቦት ጋር ግንኙት ያለው ስራ የሚሰሩ ተቋማት፣ የጽዳት ስራዎችን የሚሰሩ ተቋማትና ባለሙያዎች፣ ከድንገተኛና የእሳት አደጋ መከላከል ጋር የተያያዙ ስራዎችን የሚሰሩ ተቋማት፣ ከጥበቃና ደህንነት ጋር የተያያዙ ድርጅቶች እና ተቋማት በማንኛውም መልኩ ስራን አለመስራት፡ማቋረጥ፡ ማስተጓጎል እና መሰል ተግባራትን መፈፀም የተከለከለ ነው።

25/ It is prohibited to resign from, delay the work of or in any way obstruct the functioning of institutions which provides basic services such as electric, water, and telecom utility companies; medical institutions, banks; enterprises related with the supply of food, provision of sanitary services, fire and emergency services, security and intelligence services.

፳፮/ የደረቅና የፈሳሽ ጭነት አገልግሎትን፣ የምርት ስራን፣ የእርሻ ስራን ወይም የግንባታ ስራን ማቋረጥ፣ ማሰተጓጎል ወይም አለመስራት የተከለክለ ነው፡፡

26/ It is prohibited to stop, obstruct or suspend the transportation of liquid or dry cargo, construction, manufacturing and agricultural activities.

፳፯/ ኮቪድ-፲፱ኝና ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ ማህበረሰቡ እንዲሸበር የሚያደርግና በማህበረሰቡ ላይ ያልተገባ ሥነ-ልቦናዊ ጫና የሚፈጥር ማናቸውንም መረጃ ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡፡

## ፬. <u>የተጣሉ ግዴታዎች</u>

፩/ ማንኛውም ኮቪድ-፲፱ እንዳለበት የተጠረጠረ ሰው ወይም ወደ ሀገር የሚገባ ዓለምአቀፍ መንገደኛ መንግስት በሚያዘጋጀው ቦታ ኳራንታይን የመደረግና የኮቪድ-፲፱ ምርመራ የማድረግ ግዴታ አለበት።

፪/ ወደ ሀገር የገባ ዓለምአቀፍ መንገደኛ ኳራንታይን በሚደረግበት ጊዜ የራሱን ወጪ የመሸፈን ኃላፊነት ያለበት ሲሆን፣ መንገደኛው የመክፈል አቅም የሌለው ከሆነ መንግስት ለዚሁ ዓላማ ባዘጋጀው ቦታ እንዲቆይ ይደረጋል።

፫/ በኮቪድ-፲፱ መያዙ የተረጋገጠ ማንኛውም ሰው መንግስት በሚያዘጋጀው ለይቶ ማቆያ ክፍል የመቆየት ግዴታ አለበት።

፬/ በጉዞ ወቅት ኮቪድ-፲፱ አለበት ተብሎ የሚጠረጠር መንገደኛ ሲኖር የማጓጓዣ አንቀሳቃሹ በአቅራቢያው ላለው ወይም ለሚያርፍበት የመግቢያና መውጫ ኬላ ኃላፊ ወይም የኮቪድ-፲፱ ምርመራ ለሚያደርግ ቡድን የማሳወቅ ኃላፊነት አለበት።

፭/ ኮቪድ-፲፱ ያለበት ወይም አለበት ተብሎ የሚጠረጠር ሰው ሰለመኖሩ የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በአቅራቢያው ለሚገኙ የጤና ኃላፊዎች ወይም ለፖሊስ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

፮/ የባንክ አገልግሎት በሚሰጥባቸው አካባቢዎች፣ በገበያዎች፣ በትራንስፖርት መሳፈሪያ ቦታዎች፣ በትራንስፖርት ውስጥ፣ በሱቆች፣ በመድሀኒት መሸጫ አካባቢዎች፣ ህዝባዊ አገልግሎት በሚሰጥባቸው ቦታዎችና ሌሎች ህዝብ በሚበዛባቸው መሰል አካባቢዎች የሚገኝ ማንኛውም ሰው አፍና አፍንጫው ላይ መሸፈኛ የማድረግ ግዴታ አለበት።

27/ It is prohibited to disseminate any information about Covid-19 and related issues which would cause terror and undue distress among the public.

## 4. <u>Duties Imposed</u>

1/ Everyone suspected of being COVID-19 positive and all international passengers shall quarantined at a place designated for this purpose by the government and tested.

2/ An international passenger entering the country shall cover the cost of his quarantine and the passenger will be quarantined at a place designated by the government for this purpose if he cannot pay for his quarantine.

3/ Any person who has tested positive for Covide-19 shall have an obligation to stay in isolation facilities.

4/ A transport operator shall inform the head of the nearest entry port or to the Covid-19 screening team about any passenger suspected of being infected with Covid-19.

5/ Any person should inform the police, the Ministry of Health or the nearest health officials of any person he suspects of being infected with Covid-19.

6/ Any person who is found at banks, marketplaces, transport depots, in public transit, shops, pharmacies, places where public services are provided or any other public space where a large number of people are found is required to put on a cover on his nose and mouth.

፯/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፮ የተመለከተው የአፍና አፍንጫ መሸፈን ግዴታ ለዚሁ ዓላማ ተብሎ በፋብሪካ በተሰራ፣ በቤት ውስጥ ከተለያዩ ጨርቃጨርቆች በተዘጋጀ ወይም በማናቸውም ዓይነት ልብሶች ሊፈፀም ይችላል፡፡

፰/ ማንኛውም አገልግሎት የመንግስትም ሆነ የግል አገልግሎት ሰጪ ተቋም አገልግሎቱን ለማግኘት ወደ ተቋሙ ለሚመጡ ተገልጋዮች ቫይረሱን ለመከላከል የሚያስችሉ የንፅህና መጠበቂያ ቁሶችን ማዘጋጀትና ተገልጋዮች አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረጋቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

፱/ ማናቸውም አገልግሎት የሚሰጡ የመንግስትም ሆነ የግል ተቋማት አገልግሎት ለማግኘት ወደ ተቋማቱ የሚሄዱ ተገልጋዮች ሁለት የአዋቂ እርምጃ ተራርቀው የሚቆሙበትን ቦታ ምልክት የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

፲/ የመንግስት የኮሙኒኬሽን ባለሙያዎችና የሚዲያ ተቋማት ኮቪድ-፲፱ኝና ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚያስተላልፏቸው መረጃዎች፣ የዜና ትንተናዎች ወይም ፕሮግራሞች ሳይጋነኑ ወይም ሳይቃለሉ ተገቢውን መረጃ ወደ ሕዝቡ የማድረስ እና አላግባብ የሆነ ድንጋጤና ሽብርን የማይፈጥሩ መሆን አለባቸው::

፲፩/ ማንኛውም በፌደራልም ሆነ በክልል የሚገኙ የመንግሥትም ሆነ የግል ተቋማት በተቋሙ ስር ለሚገኙ ሰራተኞች ስለቫይረሱ አስፈላጊውን መረጃ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የማድረስ፣ በመግቢያና መውጫ በሮችና ሌሎች አስፈላጊ ቦታዎች ላይ ቢያንስ እጅ ለመታጠብ የሚያስችል ውሃና ሳሙና ማዘጋጀት ፣ በተቻለ መጠን ሌሎች የቫይረሱን ስርጭት ለመግታት የሚረዱ የጥንቃቄ ቁሳቁሶችን ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

፲፪/ ማንኛውም በፌደራልም ሆነ በክልል የሚገኙ የመንግሥትም ሆነ የግል ተቋማት በተቋሙ ስር የሚገኙ ሰራተኞች በአንድ ክፍል ውስጥ፣ በአንድ መስሪያ ቦታ ወይም በአንድ ትራንስፖርት ውስጥ ተጨናንቀውና አካላዊ ርቀትን ለመጠበቅ በማያስችል መልኩ እንዳይሰሩ ለማድረግ አስፈላጊውን ፈረቃ ማመቻቸት፤ ሰራተኞቹ ቤታቸው ሆነው

7/ The obligation under Sub-Article (6) of this Article can be discharged using the coverings manufactured for this purpose, homemade masks or clothing of any kind,

8/ Any public or private service provider should provide sanitary materials useful for preventing the spread of the virus and ensure that customers are taking the necessary precautionary measures.

9/ Any public or private service provider should mark spots where customers could stand maintaining a two adult stride distance.

10/ Public communication professionals and media outlets have a duty to ensure that the information, analysis, or programme that they provide to the public relating to COVID-19 is without exaggeration, appropriate and not prone to cause panic and terror among the public.

11/ All federal or regional public or private organizations shall use various mediums to make accessible to their employees information regarding COVID-19; provide at least water and soap for washing hands at their gates and to the extent possible other materials useful to prevent the spread of the virus.

12/ All federal or regional, public or private organizations shall ensure that employees working in one room or place of work or using a common transportation means will not be forced to be confined conditions that make it impossible to maintain social distance and towards this end shall allow employees to work in shifts or to work from home or take paid leave.

የሚሰሩበትን ሁኔታ ወይም እረፍት በመውሰድ ስራ ቦታ እንዳይመጡ የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት።

፲፫/ ማንኛውም የፌደራልም ሆነ የክልል የመንግስት ተቋምና በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፮/፪ሺ፲፩ መሰረት የሚተዳደሩ ሰራተኞችን የሚያስተዳድር የግል ድርጅት ሰራተኞቹ ወደ ስራ ቦታ ለመሄድ ትራንስፖርት መጠቀም አስፈላጊ ከሆነ በስራ ላይ ለሚገኙ ሰራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት።

፲፬/ ፖሊስ ኮሚሽን ወይም ማረሚያ ቤት ተጠርጣሪዎች ከጠበቆቻቸው ጋር የሚገናኙበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት።

፲፭/ ማንኛውም የቤት፣ የሆቴል፣ የአፓርታማ፣ የተሽከርካሪ፣ የአዳራሽ ወይም የማንኛውም ንብረት ባለቤት መንግስት የኮቪድ-፲፱ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ ለሚያደርገው ጥረት አስፈላጊ የሆነ ንብረቱን ለዚህ ዓላማ አገልግሎት ላይ እንዲውል በሚኒስትሮች ኮሚቴ ወይም ኮሚቴው ውክልና በሰጠው የመንግስት አካል ሲወሰንና ሲጠየቅ ንብረቱን ለዕለት ከዕለት ፍጆታው የሚጠቀምበት ካልሆነ በስተቀር ውሳኔውን ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለበት።

፲፮/ ማንኛውም አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ ድርጅት፣ የኮቪድ-፲፱ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ ለሚደረገው ጥረት አስፈላጊ የሆነ አገልግሎት እንዲሰጥ፣ አገልግሎቱን እንዲያሰፋ፣ ምርት እንዲያመርት፣ የሚያመርተውን ምርት መጠን እንዲጨምር፣ አዲስ ምርት ዓይነት እንዲያመርት ወይም ምርቱን መንግስት በሚወስነው ተመጣጣኝ ዋጋ ለመንግስት፣ ለሸማቾች ወይም ለህብረት ስራ ማህበራት እንዲሸጥ በሚኒስትሮች ኮሚቴ ወይም ኮሚቴው ውክልና በሰጠው የመንግስት አካል የሚሰጠውን ትዕዛዝ ተግባራዊ ማድረግ አለበት።

13/ All Federal or Regional public organizations and private organizations which administer employees based on labour proclamation No 1156/2019 shall provide appropriate transportation for employees when such transportation service is necessary. .

14/ Police Commissions and Prison Administrators shall facilitate conditions to let the suspected persons and lawyers meet.

15/ The owner of any house, hotel, apartment, vehicle, or any other property shall avail to the government such property if the Ministerial Committee or an entity delegated for this task by the Committee determines that the property is necessary in the effort to counter and control the spread of COVID-19 and mitigate its impact, unless the property is needed by the owner for his daily use.

16/ Any service provider or manufacturer shall comply with the instruction of the Ministerial Committee or an entity delegated for this task to provide a service, expand its service, manufacture a new kind of product, increase the production of an item or sell at a reasonable price to the government, cooperatives or consumer associations any product that is necessary in the effort to counter and control the spread of COVID-19 and mitigate its impact.

፲፯/ ሆቴሎች ለደንበኞቻቸው አገልግሎት በሚሰጡበት ጊዜ የእጅ መታጠቢያ ውሀና ሳሙና የማቅረብ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን፣ የሆቴሉ ተጠቃሚዎችም እጃቸውን መታጠባቸውንና አስፈላጊውን ንፅህና አጠባበቅ ሥርዓት ተግባራዊ ማድረጋቸውን የማረጋገጥ እንዲሁም ደንበኞች ከተጠቀሙ በኋላ የተገለገሉባቸውን ጠረጴዛዎች፣ ወንበሮችና ሌሎች እቃዎች የማከም ግዴታ አለባቸው።

፲፰/ ማንኛውም በስራ ላይ ያለ፣ ጡረታ የወጣ ወይም በትምህርት ላይ ያለ የጤና ወይም የሌላ ሙያ ባለቤት ወይም ማንኛውም ዜጋ የኮቪድ-፲፱ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ በሚደረገው ጥረት አስተዋፅዖ እንዲያደርግ በመንግስት ጥሪ ሲደረግለት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

17/ Hotels, restaurants and cafes shall provide water and soap to their customers and ensure that their customers have washed their hands and carried out the necessary sanitary precautions and should disinfect tables, chairs and other goods that have been used by patrons.

18/ Any medical or other profession in active service, in retirement or in training or any citizen has a duty to comply with any request the government might issue to in the effort to counter and control the spread of COVID-19 and mitigate its impact.

## ፭. <u>የሚኒስትሮች ኮሚቴ ስለመቋቋምና ሥልጣንና ተግባር</u>

፩/ የሚኒስትሮች ኮሚቴ ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት የሚመራ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የሆነ ኮሚቴ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/ የኮሚቴው አባላት ስብጥር እና ብዛት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይወሰናል።

፫/ ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የኮቪድ-፲፱ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚሰራውን ስራ በበላይነት ይመራል ፣ ያስተባብራል፤

ለ) የቫይረሱን ሥርጭት በተመለከተ አስፈላጊውን መረጃና ማስረጃ ይሰበስባል፣ ይተነትናል፤ በትንተናው ላይ ተመስርቶ አስፈላጊውን አቅጣጫ ይሰጣል፤

## 5. <u>Establishment, powers and responsibilities of Ministerial Committee</u>

1/ A Ministerial Committee, herein after referred to as “Committee” to be chaired by the Deputy Prime Minister and Accountable to the prime minister is hereby established.

2/ The composition and number of members of the Committee shall be decided by the Prime Minister.

3/ The Committee Shall have the following powers and responsibilities:

a) Oversee and coordinate the effort to counter and control the spread of COVID-19 and mitigate its impact.

b) Compile, analyse the necessary data regarding the spread of the virus and on the basis of such analysis issue the necessary directions;

ሐ) በስሩ የተለያዩ ንዑሳን ኮሚቴዎችን በፌደራል፣ በክልል፣ በከተማና ወረዳ ደረጃ ያቋቁማል፣ አስፈላጊውን መረጃ፣ ማስረጃና የስራ ስምሪት ይሰጣል፣ ሪፖርታቸውን ይገመግማል አቅጣጫ ያስቀምጣል፤

መ) በዚህ ደንብ ላይ የተደረጉ ክልከላዎችና የተጣሉ ግዴታዎች ቀሪ የሚሆኑበትን አግባብ እየገመገመና ችግሩ እየቀነሰ ከሄደ ክልከላዎችና የተጣሉ ገደቦች ቀሪ እንዲሆኑ ይወስናል፣ በሚመለከተው ንዑሳን ኮሚቴ በኩል ለማህበረሰቡ እንዲደርስ ያደርጋል፤

ሠ) የቫይረሱ ስርጭት እየሰፋ እና እየጨመረ በመሄዱ ምክንያት ተጨማሪ ክልከላዎችንና የሚጣሉ ግዴታዎችን በደንብ መደንገግ አስፈላጊ መሆኑን ባመነበት ጊዜ አስፈላጊው ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲቀርብ ትእዛዝ ይሰጣል፤

፬/ የኮሚቴውን ስብሰባ እና ዝርዝር የአሰራር ሥነ-ሥርዓት በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል፤

፭/ ኮሚቴው ለክልሎችና ለከተማ መስተዳድሮች ለተመሳሳይ አደረጃጀቶች ስራቸውን በተመለከተ መመሪያና ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ፮. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፩/ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህጉና ሌሎች አዋጆች ላይ የተመለከቱ የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነታቸው ታግዷል።

፪/ የክልልና ፌደራል ፍርድ ቤቶች ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ጉዳዮችን፣ ከምርት መደበቅና ዋጋ መጨመር ፣ ከሕገወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር እና የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ የወንጀል ድርጊቶችን በተመለከተ በአፋጣኝ ውሳኔ የሚሰጡ ችሎቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት አለባቸው።

c) Establish various sub-committees at federal, region, municipal and woreda level, provide the necessary information, direction and assignment to the committees and evaluate their report.

d) Evaluate the need to lift prohibitions and duties imposed under this Regulation and if the threat of the pandemic decrease, decide to lift partially or in full the prohibitions and duties imposed under this Regulation, and notify to to the society through appropriate sub-committee.

e) Present to the Council of Ministers, additional restrictions that it is deems necessary if it is convinced that the spread of the virus is increasing and additional restrictions are needed.

4/ The working procedure of the committee shall be decided by a directive it shall issue.

5/ The committee may delegate its power to and cause the establishment of similar structures at regions and municipalities.

## 6. Miscellaneous provisions

1/ The criminal procedure code and criminal procedural provisions in other laws are suspended.

2/ Regional and Federal Courts have an obligation to establish dedicated benches that would give decisions in an expedited manner with regard to cases arising in relation to the state of emergency proclamation, hording and other unfair trade practices, illicit tracking in arms and contraband goods .

፫/ በንዑስ አንቀጽ ፪ የተመለከቱት ችሎቶች ተግባራዊ የሚያደርጉትን ሥርዓት በተመለከተ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፬/ በፌደራል እና በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረት የክልል እና የፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍትሃ ብሄር ጉዳዮችን በከፊልም ሆነ ሙሉለሙሉ ማስተናገድ ሊያቆሙ ይችላሉ።

፭/ በኮቪዲ-፲፱ ምክንያት ህይወቱ ያለፈ ማንኛውም ሰው የቀብር ሥርዓቱ የሚፈጸመው በመንግስት አማካኝነት ለዚሁ ዓላማ በተለዩ ቦታዎች ሲሆን በቀብሩ ላይ የሚገኘውን የሰው ብዛትና የቀብሩ ዝርዝር አፈፃፀም በመመሪያ ይወሰናል።

፮/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፫ ፬፣ ፭ እና ፮ ከተመለከቱት ተሽከርካሪዎች ውጪ ያሉትን የመጓጓዣ አይነቶች በተመለከተ የሚጣሉ ክልከላዎች በሚወጣ መመሪያ ይወሰናሉ።

፯/ በዚህ ደንብ የተከለከሉ ተግባራትን የፈፀመ ወይም የተጣሉ ግዴታዎችን የተላለፈ ማንኛውም ሰው በአዋጁ ላይ የተመለከተው ቅጣት ተፈፃሚ ይሆንበታል፡፡

## ፯. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

የሚኒስትሮች ኮሚቴ አዋጁን እና አዋጁን ተከትሎ የወጣውን ይህን ደንብ ለማስፈፀም ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ያወጣል::

## ፰. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ሚያዚያ ፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ/ም ጀምሮ አዋጁ በስራ ላይ ባለበት ጊዜ ተፈፃሚ ይሆናል::

**አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ/ም**

**አብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

3/ The Federal Supreme Court may issue a directive regarding the working procedure of benches indicated under Sub-Article (2).

4/ Based on the decision of Federal and Regional Supreme Courts, the federal and regional judiciary may partially or fully cease from adjudicating civil cases.

5/ The interment of any person who has died from COVID-19 shall be carried out by the government at places designated for this purpose in accordance with directives limiting the number of people who can attend the funeral and providing other details concerning the interment.

6/ Restrictions regarding modes of transportation other than those mentioned under Article 3 (4), (5) and (6) of this Proclamation will be determined through a directive to be issued.

7/ Any person who commits acts prohibited or violates the duties imposed in this Regulation shall be punished in accordance with the Proclamation.

## 7. Power to Issue Directives

The Ministerial Committee may issue directives for the implementation of this Regulation and the Proclamation.

## 8. Effective Date

This Regulation shall be effective from 11th day of April, 2020 it has been adopted by the Council of Ministers throughout the period in which the proclamation remains in force.

**Done at Addis Ababa, on this 20th day of April 2020.**

**ABIY AHMED (PH.D.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**